# የትግራይ ኮማንድ ፖስት

የትግራይ ኮማንድ ፖስት ከመጋቢት 19 ቀን 2013 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ መመሪያ (መመሪያ 1/2013) አውጥቷል።

በዚህ መመሪያ በክልሉ የነበረው ሰዓት እላፊ ክልከላ ከምሽቱ 1 ሰዓት ወደ ምሽት 2 ሰዓት ተሻሽሏል።

የተጣሉ ክልከላዎች

- መንግስት ሰራተኛ ስራው ላይ እንዳይገኝ አሉባልታ መንዛት ክልክል ነው።
- ማንኛውም ሰው በፅሁፍ፣ በቃል፣ በምስል፣ በአካል እንቅስቃሴ ወይም በሌላ ድርጊት በመንግስት ተቋም፣ ግለሰብ ወንጀል እንዲፈፀም ማነሳሳት/የወንጀል ተግባር የሚፈፅሙትን ማሞካሸት ክልክል ነው።
- የህዝቡ ደህንነት ወይም ግለሰብ እንዲሁም ንብረት አስጊ አደጋ እንደሚገጥመው በተለይ የሰው ግድያ፣ ቃጠሎ፣ ውጊያ እንደሚደርስበት የሃሰት ወሬ በማሰራጨት ህዝቡ እንዲፈራ እና እንዲሸበር ማድረግ የተከለከለ ነው።
- በመንግስት፣ በኃላፊዎች እና ሰራተኞች ላይ ሀሰተኛ ወሬ፣ ጥርጣሬ፣ ሀሰተኛ ስሜትን የሚፈጥር/የሚያሰራጭ ከዚህ የተነሳ የህዝቡን አስተሳሰብ ማዛባት፣ ማጉደል፣ ማናጋት፣ ጥላቻ ማስፋፋት የተከለከለ ነው።
- የህዝቡን ኑሮ እና ፀጥታ ለማናጋት ያለሙ/የሚያናጉ ሀሰተኛ/የተጋነነ/የተዛባ ወሬ መግለፅ/ማሰራጨት የተከለከለ ነው።
- የህዝቡን ህይወት ለማዳን እየቀረቡ ያሉ እቃዎችን መዝረፍ ክልክል ነው።
- አግባብ ያላቸውን ደንቦች አለማክበር፣ አስፈላጊ ጥንቃቄ ባለማድረግ የህዝብ መተላለፊያ መንገድ/ለህዝብ ክፍት በሆኑ ቦታዎች የእሳት አደጋ ሊያስነሳ የሚችል ማንኛውም አይነት ነገር ያስቀመጠ፣ መንገድ የቆፈረ፣ ያበላሸ ወይም ትክክለኛ አገልግሎት እንዳይሰጡ ማድረግ የተከለከለ ነው።
- የህዝብ ማጓጓዣ አግልግሎት ለመስጠት ፍቃድ ይዘው በተዛባ ወሬ እና ባልተረጋገጠ ስጋት ወይም ሆን ብሎ የመጓጓዣ አገልግሎት ያስቆመ ታክሲ፣ ባጃጅ፣ አውቶብስ አሽከርካሪዎች ስራ ማቆም ክልክል ነው።
- የንግድ ፍቃድ አውጥቶ በንግድ ስራ የተሰማራ ማንኛውም ነጋዴ የንግድን ስርዓት በሚጋጭ መልኩ ስራ ማቆም/አድማ ማድረግ/ ሌሎችን ማነሳሳት ክልክል ነው።
- ህጋዊ እውቅና ያለው ተቋም ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ከንግድ ተቋም ስራዎች በማያያዝ የንግድ ተቋሙን ህጋዊ ግዴታ መጣሰ ወይም በሀሰተኛ ወሬ ስራ መዝጋት የተከለከለ ነው (ከድርጅቱ ላይ የሚወሰድው እርምጃ እንዳለ ሆኖ ኃላፊውም፣ ሰራተኛውም ላይ እርምጃ የሚያስወስድ ነው)
- ህጋዊ እውቅና ያለው ተቋም አክሲዮን፣ ማህበር፣ ባንክ፣ ኢንሹራንስ፣ ስራ ያቆመ፣ አገልግሎት ማቆም የተከለከለ ነው።

- በመገናኛ ብዙሃን የህዝቡን ሰላማዊ አኗኗር፣ ፀጥታ ለማናጋት ዓላማ ያደረጉ ማንኛውም የተጋነነ እና ሀሰተኛ ወሬ ማውራት ማሰራጨት የተከለከለ ነው (የክልሉ ሚዲያ፣ ሀገራዊ ሚዲያዎችም ጭምር ይመለከታል ጋዜጠኞች፣ ኃላፊዎች ተጠያቂ ይሆናሉ)

- የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ግብረኃይል የወሰናቸውን ውሳኔዎች እና ትዕዛዞችን መተላለፊ/መቃወም ክልክል ነው።

- ለማንኛውም ኢ-መደበኛ ድርጅት አባል በመሆን ህዝቡን ለአድማ/አመፅ ማነሳሳት፣ በማንኛውም መገናኛ ብዙሃን ህዝባዊ እንቢታን መጥራት/መሳተፍ/ሌላ ሰው እንዲሳተፍ ማነሳሳት ክልክል ነው።

- ሲቪል ሆኖ የሀገር መከላከያ መልበስ/መለዮ ለብሶ መገኘት ወይም ይዞ መገኘት የተከለከለ ነው።

- ከምሽት 2 ሰዓት እስከ ንጋት 12 ሰዓት ከቤት ውጪ መንቀሳቀስ ክልክል ነው።

የህግ እርምጃዎች

- ክልከላዎቹን ያለፈ ከ3 ዓመት እስከ 5 ዓመት እስራት ይቀጣል።

- የህግ ሰውነት ባላቸው አካላት /ድርጅቶች መመሪያዎቹ ከተጣሱ ከ50 ሺህ ብር እስከ 100 ሺህ ብር የገንዘብ ቅጣት ይጣልባቸዋል።

- ስራ የማቆም አድማ ያካሄደ ተሽከርካሪ ከአሽከርካሪው ቅጣት በተጨማሪ ባለቤቱ ከ5 ሺህ እስከ 10 ሺህ ብር የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል።

- መመሪያውን የጣሰ የተቀመጠውን ቅጣት የሚቀጣ ከመሆኑ ባሻገር አስተዳደራዊ ቅጣቶችም ሊጠብቁት ይችላሉ።